**የእስራኤል ባንክ**
የቃል አቀባይ እና የኢኮኖሚ መረጃ ፅህፈት ቤት

ዲሴምበር 1, 2022

ጋዜጣዊ መግለጫ:

# የእስራኤል ባንክን ወይም የባንክ ኮርፖሬሽኖችን በመምሰል የሚፈፀሙ ማጭበርበሮችን በሚመለከት ለህብረተሰቡ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ

የባንክ ሱፐርቪዥን መምሪያ የባንክ ተወካዮችን፣ የክሬዲት ካርድ ኩባንያዎችን፣ የእስራኤልን ባንክ፣ የእስራኤልን ፖሊስ እና ሌሎችንም በመምሰል ወንጀለኞች ከደንበኞች ገንዘብ ለመቀበል በማሰብ የማጭበርበር ድርጊቶችን ለመፈፀም እየሞከሩ እንደሚገኙ ህብረተሰቡን እያነቃ ይገኛል። አንዳንድ ጊዜ እነዚህ ወንጀለኞች የፖሊስ መታወቂያ ወይም ከእስራኤል ባንክ የተፃፈ ደብዳቤን የመሳሰሉ ሀሰተኛ ማንነታቸውን የሚያረጋግጥላቸው ሀሰተኛ ሰነዶችን ይልካሉ። የማጭበርበር ሙከራዎቹ ወንጀለኞቹ የስልክ ንግግሮችን፣ አጭር የፅሁፍ መልዕክቶችን እና ኢሜይልን የመሳሰሉ የተለያዩ የመገናኛ መንገዶችን በመጠቀም የባንኩን ደንበኞች ማግኘትን ያካትታሉ። ማስታወቂያዎቹ የሚላኩት ባንክን ከመሳሰለ ነን ብለው እያስመሰሉ ከሚገኙት ተቋም አድራሻ ነው። በማጭበርበሩ ወቅት የባንክ ወይም የእስራኤልን ባንክ አድራሻ የሚመስሉ ሀሰተኛ አድራሻዎችን እና የስልክ ማውጫዎችን ጥቅም ላይ የሚያውሉ ሲሆን ሌላ ጊዜ ደግሞ ማስታወቂያዎቹ ህጋዊ የሚመስል ድረገፅ አገናኝንም ያካትታሉ።

ወንጀለኞቹ ከሂሳቡ ባለቤት ጋር ግንኙነት ከፈጠሩ በኋላ ገንዘብ ከሂሳቡ ላይ እንዲወጣ የሚደረግበትን የግል ዝርዝር መረጃ ወይም የገንዘብ መረጃ እንዲልክላቸው ወይም እንዲያስተላልፍላቸው የሂሳቡን ባለቤት ይጠይቃሉ። ወንጀለኛው ሊጠይቀው የሚችለው መረጃ የሚከተሉትን ያካትታል፡ የግል ዝርዝር፣ የሂሳብ ዝርዝር፣ የክሬዲት ካርድ ዝርዝር እና በሂሳቡ ወይም በክሬዲት ካርዱ ባለቤት በተንቀሳቃሽ ስልኩ አማካኝነት የተቀበለው ኮድ።

አንዳንድ ጊዜ ወንጀለኞቹ የተጠየቀው መረጃ ሂሳቡን ከወንጀለኞች ድርጊት ለመከላከል ወይም የባንኩ ወይም የክሬዲት ካርዱ ኩባንያ ሰርቨር ላይ የተከሰተ ብልሽትን ለማስተካከል የተጠየቀውን መረጃ የሚፈልግ አስቸኳይ ምላሽ ለመስጠት እንደሚያስፈልግ በመግለፅ በዛቻ ወይም ደንበኛውን

የማስፈራራት እና የመገፋፋት ስትራቴጂዎችን በመጠቀም ዝርዝሩን ከደንበኞች ይጠይቃሉ። ወንጀለኞቹ የሚጠቀሙበት ሌላው ስትራቴጂ ገንዘብ እንደሚቀበሉ ቃል መግባት፣ ሎተሪ እንዳሸነፉ ማሳወቅ፣ ወይም ሳቢ ኢንቨስትመንት ለማድረግ የባንክ ሂሳቡን ማግኘት እንደሚያስፈልጋቸው በመግለፅ ነው።

ህብረተሰቡ ንቃቱን እንዲጨምር እና የግል ወይም ሚስጥራዊ መረጃ እንዳይሰጥ ይጠየቃል። የእስራኤል ባንክ፣ የባንክ ኮርፖሬሽኖች እና የክሬዲት ካርድ ኩባንያዎች የግል ወይም የግል ኮድን የያዘ አጭር የፅሁፍ መልእክትን የመሰሰለ ሚስጥራዊ ዝርዝር መረጃ ወይም የማረጋገጫ እና የመለያ መንገድን ግንኙነቱን ላደረገው ሰው እንዲላክ ማድረግን ጨምሮ የገንዘብ ዝርዝር መረጃ እንዲልኩ ለመጠየቅ ከዜጎች ጋር አይገናኙም።

የማጭበርበር ድርጊት ሰለባ እንደሆኑ ከጠረጠሩ በቀጥታ የባንኩን ኮርፖሬሽን የጥበቃ መምሪያ ወይም እንባጠባቂን በተቻለ ፍጥነት እንዲያገኙ እንመክራለን። ምላሽ የማያገኙ ወይም ምላሹ አጥጋቢ የማይሆን ከሆነ በጉዳዩ ላይ ያለዎትን ቅሬታ ለመግለፅ የባንኩን ሱፐርቪዥን መምሪያ ማግኘት ይችላሉ።

**የባንክ ሂሳብዎን ለመጠበቅ የሚያስችሉ ምክረ ሀሳቦች፡**

- በተቀበሉት አጭር የፅሁፍ መልእክት ወይም ኢሜይል በኩል ከባንክ ሂሳብዎ ጋር አይገናኙ።
- እየተጠቀሙበት ያለውን የድረገፅ አድራሻ ይፈትሹ እና በተለይ አድራሻውን ያገኙት በመፈለጊያ ማሽን ከፈለጉ በኋላ ከሆነ ስሙ በትክክል መፃፉን ያረጋግጡ።
- ቁጥሩን ከባንኩ ድረገፅ ላይ ራስዎ ፈልገው ካገኙ በኋላ ብቻ የመለያ ዝርዝሮችን ወደ ባንኩ የጥሪ ማዕከል በመደወል ይስጡ።
- በአጭር የፅሁፍ መልእክት ወይም በኢሜይል በኩል ዝርዝሮችን እንዲያሟሉ ሲጠየቁ የክሬዲት ካርድ ወይም የመለያ ኮድ ዝርዝሮችን አይስጡ። ባንኩ ወይም የክሬዲት ካርድ ኩባንያው በስልክ ውይይት ወቅት ደንበኛው ራሱ ካላነሳሳ በስተቀር የኮድ ዝርዝሮችን አይጠይቅም።
- ስህተት የሰሩ ከሆነ እና ለወንጀለኛ ዝርዝሮችን ሰጥቻለው ብለው ከሰጉ ወዲያውኑ ለባንኩ ኮርፖሬሽን በመደወል ሪፖርት ያድርጉ።
- አጠራጣሪ የገንዘብ ግብይቶችን ወይም ልዩነቶችን ለማግኘት በሂሳብዎ እንቅስቃሴ እና የገንዘብ ግብይትን በየጊዜው ይፈትሹ።
- ማንኛውም ጥርጣሬ የሚኖር ከሆነ፣ ምንም ዓይነት ጥርጣሬ የማይኖር ከሆነ-እና ማንኛውንም መልእክት ወይም የስልክ ጥሪ አለመመለስ ወይም ተያያዥነት ካለው ባንክ ወይም ኩባንያ ሳያጣሩ በፊት ማንኛውንም አገናኝ ጠቅ ያለማድረግ መልካም ነው።